# ዝክረ ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ



ዶ/ር.ተስፋዬ ደበሳይ
Dr. Tesfaye Debessay
የኢሕአፓ አመራር አባል (EPRP Leadership member)

በሀገራችን ኢትዮጵያ ሰሜን ምሥራቅ ትግራይ ክፍለ ሀገር፤ በአጋሜ አውራጃ፤ በኢሮብ ወረዳ እምትገኝ፤ ዓሊተና እምትባል መንደር በጣም ደሀ ከሚባሉ ቤተሰብ ክፍል ከአባቱ ከአቶ ደበሳይ ካሕሳይና ከእናቱ ከወ/ሮ ምህረታ ዓዶዑማር በ1933 ዓ.ም. ሕፃን ተስፋዬ ተወለደ።

ለአባትና ለእናቱ ብቸኛ የበኩር ወንድ ልጃቸው ሲሆን ከሱ በኋላ የተውለዱት ስድስቱም ሴቶች ሲሆኑ አባትና አምስቱ እህቶቹ በሕይወት አሉ።

ተስፋዬ ደበሳይ ዕድሜው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ በተወለደባት መንደር ዓሊተና ትምህርት ቤት ባለመኖሩ ለመማር የነበረው ዕድል እጅጉን የጨለመ ነበር። ቀረብ ያለ ትምህርት ቤት በጊዜው የነበረው ከዓሊተና 35 ኪሎ ሜትር ገደማ እርቀት ላይ አዲግራት ከተማ ውስጥ ነበር። በዚህ ምክንያት ሕፃኑ ተሰፋዬ ዕድሜው ለትምህርት እንደደረሰ ትምህርት ሊያገኝ ባለመቻሉ ወላጆቹን ትምህርት ወደሚገኝበት ቦታ ወስደው ወደ ት/ቤት እንዲያሰገቡት ሌት ተቀን ይጨቀጭቃቸው እንደነበር ወላጆቹና ጎሮቤቶቻቸው ይመሰክራሉ። ወደ ሌላ ቦታ ወስደው ት/ቤት እንዳያስገቡት ግና በጣም ድሆች ነበሩ። ስለዚህ ተሰፋዬ ለመማር የነበረው ዕድል በጣም የተወሰነ፤ የመነመነ ነበር።

ተስፋዬ ገና በልጅነቱ ለመማር ከነበረው ጉጉት የተነሳ ውትወታውን ሳያቋርጥ ሊገኝ የሚችለውን አማራጭ ሁላ ያሰላስል ነበር። ተስፋዬ ዕድሜው አሥር ዓመት ገደማ ሲሆነው በሌላ አከባቢ ይኖሩ የነበሩ፤ ከወላጆቹ ሻል ያለ ኑሮ የነበራቸውና የራሳቸው ልጆች ወዳልነበራቸው አክስቱ ሄዶ ለትምህርት ያለውን ፍላጎት ገልጾ፤ ወላጆቹ ግና ከድህነታቸው የተነሳ ለት/ቤት ሊከፍሉለት እንደማይችሉ በማስረዳት ያስተምሩት ዘንድ ተማጸናቸው። የተስፋዬን የትምህርት ፍላጎትና ጉጉት የተገነዘቡት አክስቱ ያለምንም ማመናታት የሚከፈለውን ከፍለው በዓዲግራት ከተማ በሚገኝ የካቶሊክ ት/ቤት አስገቡት።

በተፈጥሮው ለየት ያለ ባህርይ እንደነበረው የሚነገርለት ተስፋዬ በአገኘው ዕድል ለመጠቀም እርሳስና ደብተሩን ታጥቆ ተነሳ። ጊዜም ሳይወስድ በገባበት የካቶሊክ ት/ቤት የሚመሰገን ጎበዝና ምርጥ ተማሪ ሆነ። በዓመት አንድ ሳይሆን ሁለት ክፍሎችን መዝለል ለተስፋዬ የተለመደ ነበር። ተስፋዬና ትምህርት፣ ትምህርትና ተስፋዬ ገና በለጋ ዕድሜው የተዋሃዱ መሆናቸውን በችሎታውና በጉብዝናው አስመሰከረ። ተስፋዬ የመጀመርያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እዛው በካቶሊክ ት/ቤት እጅግ በጣም ጥሩ ውጤት በማምጣት ጨረሰ።

በዓዲግራት የምትገኘው የካቶሊክ ት/ቤት የተመሠረተችበት ዋና ዓላማ ተማሪዎቹዋን ለመንፈሳዊ ትምህርት ማዘጋጀት ስለነበረ የትምህርት ሥርዓትዋ ረዘም ላለ ጊዜ ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሥርዓት ጋር ሳይስተካከል ቆይቶ ነበር። ስለዚህ ለመጀመርያ ጊዜ ተማሪዎቿ በመንግሥት በሚሰጡ ብሔራዊ ፈተናዎች እንዲሳተፉ የፈቀደችው በአጋጣሚ ተስፋዬ በ8ኛ ክፍል በነበረበት ጊዜ ነበር። ይህም ቀደም ብሎ የታሰበበት ጉዳይ ሳይሆን ውሳኔው የተደረገው እነ ተስፈዬ 8ኛ ለመጨረስ ጥቂት ወራት ሲቀራቸው ነበር። ስለዚህ ያኔ በዛች ት/ቤት በስምንተኛ ክፍል የነበሩ ተማሪዎች ለብሔራዊ ፈተና በሚገባ ሳይዘጋጁ ነበር በከተማዋ ወደ ሚገኝ የመንግሥት ትምህርት ቤት (አግአዚ) ተወስደው

በፈተናው የተሳተፉት። ተማሪዎቹ በፈተናው የተሳተፉት በድንገት በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ በመሆኑ ሌሎች በሙሉ ሲወድቁ ወጣቱ ተስፋዬ ግን ብቻውን አመርቂ ውጤት በማምጣት አለፈ፤ ለዚህም አመርቂ ውጤት ያበቃው ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ ጥሩ አንባቢና አጥኚ ስለነበረ ነው።

ታዳጊ ወጣቱ ተስፋዬ በትምህርት ቤቱ የሚታወቀውና የሚደነቀው በፈተናዎች በሚያመጣው ነጥብ ወይም የክፍል ውጤት ብቻ አይደለም፤ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎችና አስተማሪዎች በተሰፋዬ የሚደነቁት ወደር የሌለው አንባቢ በመሆኑ ነበር። ትምህርት ቤቱ መጻህፍት ቤት (ላይብረሪ) አልነበረውም። በዛን ጊዜ ላይብረሪ የሚባል ነገር በከተማዋ ፈጽሞ አይገኝም። ሆኖም ዶር ተስፋዬ ከአስተማሪዎችና ከሌሎች ምሁራን እየተዋሰ ሁል ጊዜ መጻሕፍትና መጽሔቶችን ሲያነብ ይታያል። ይስተዋላል። አንዳንድ ሥነ ጽሑፍ ከየት እንደሚመጣለት እኛ ተማሪዎች ብቻ ሳንሆን መምህራን ሁሉ ሳይቀሩ ይገርማቸው ነበር። በወቅቱ፤ በ1950ዎች አከባቢ የማይገኙና ያልተለመዱ 'ታይም መጋዚን' (Times) እና 'ንዩስ-ዊክ' (News Week) መጽሄቶችን ይዞ ይታይ ነበር።

"አንድ አቶ አሰፋ ሱባ የሚባሉ በዛ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ አስተማሪ የነበሩ በጣም አዋቂ ሰው "ይህ ብርቅ ተማሪ (ተስፋዬ) የት እንደሚደርስና ለወደፊቱ ምን እንደሚሆን ለማየት ያለኝን ጉጉት ልቆጣጠረው አልችልም" ሲሉ አስታውሳለሁ።" አቶ ግርማይ ተስፋ ጊዮርጊስ የዶክተር ተስፋዬ አብሮ አደግ ጓደኛ

"አንዳንድ በዛን ጊዜ፤ ምንም ዓይነት መገናኛ ብዙሃን የማይደርሱበት አከባቢ ከመጀመርያ ደረጃ ተማሪ የማይጠበቁ ጠባዮች ይታዩበት ነበር። ጊዜው ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ከባዕድ አገዛዝ ነፃ የሚወጡበት ጊዜ ስለነበረ ዜናውን እየተከታተለ ሌሎች ተማሪዎች እንዲያውቁት ያደርግ ነበር። ከትምህርት ነፃ ስንሆን እሱ ወዳለበት እየሄድን ከበብ አድርገነው ጥያቄዎች ስናቀርብለት ትዝ ይለኛል። ስለ ጋናና ሌሎች አዲስ ነፃ የወጡ የአፍሪካ አገሮች፣ በተለይ ስለ አልጀርያ ህዝብ የነፃነት ትግል ወዘተ ቆሞ በማራኪ አንደበቱ ሲገልፅልን የነበርንበትን ቦታ ሳይቀር አስካሁን አስታውሳለሁ። ስለ አልጀርያ ህዝብ ትግል ሲገልጽ በዛ አጋጣሚ የፈረንሳይ አብዮትን በሚመለከትም መግለጫ ሰጠን። እኔ ለመጀመርያ ጊዜ ስለ ፈረንሳይ አብዮት የሰማሁት ያኔ ከሱ ነበር። ገና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለ የተስፋዬ ሁኔታ አስተማሪ እንጂ ተማሪም አይመስልም ነበር።" አቶ ግርማይ ተስፋ ጊዮርጊስ

ተስፋዬ በስምንተኛ ክፍል የሚሰጠውን ብሔራዊ ፈተና እንዳለፈ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መቀሌ ውሰጥ ወደ ሚገኘው ዮሐንስ አራተኛ ሄዶ የዘጠነኛ ክፍል ያጠናቀቀው እዛ ነበር። ያኔ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መቀሌ በስተቀር በሌሎች የትግራይ ከተሞች አልነበረም። ከዝግ ካቶሊካዊ ትምህርት ቤት ወጥቶ በመቀሌ የተማረበት ጊዜ ታዳጊው ተሰፋዬ ከብዙዎች ለህዝባቸውና ለሀገራቸው ከሚቆረቆሩ መምህራንና ተማሪዎች የመተዋወቅ ዕድል እንዳገኘ ይናገር ነበር። ከተለያየ ገጠር የመጡ ድሃ ተማሪዎች ለቤት ኪራይና ኑሮ እየከፈሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመቀጠል የነበረባቸው ችግር ምን ያህል አስቸጋሪና አሳዛኝ መሆኑን በዚሁ የመቀሌ አንድ ዓመት ቆይታው ግንዛቤ ሊያገኝ አስችሎታል። ተስፋዬ ደበሳይ በመቀሌ ያለውን የሕይወት ውጣ ውረድና ችግር ከተገነዘበና የወደፊት ዕድሉንም በውጭ አገር ለመማር ከአለው ፍላጎት በመነሳት፤ አማራጩ በፊት ወደ ነበረበት የካቶሊክ ትምህርት ቤት መመለሰ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር የመላክ ዕድሉን ከፍ ሊያደርገው እንደሚችል በመረዳት ካቶሊካዊቷ ትምህርት ቤት፡ ዓዲግራት ተመለሰ።

ተስፋዬ ዘጠነኛውን ክፍል በመቀሌ ዓፄ ዮሐንስ አራተኛ ካጠናቀቀ በኋላ እንደገና ወደ ዓዲግራቷ ካቶሊካዊት ት/ቤት ተመልሶ እንደገመተውና ተስፋ እንዳደረገው ወደ ጣሊያን አገር እስከተላከበት ጊዜ ድረስ ትመህርቱን የቀጠለው እዛው ነበር። እንደ አቶ ግርማይ አባባል "በዚያን ጊዜ..." ይላሉ "በዚያን ጊዜ ከመቀሌ የተመለሰበት ቀን በትምህርት ቤቱ አለቃ አሰባሳቢነት በአንድ ትልቅ ክፍል ተሰብስበን ቆይተን ተሰፋዬን ተነስተን በጭብጨባ ስንቀበለው ትዝ ይለኛል። በክፍሉ ያንድ ሀገር መሪ የገባ ነበር የሚመሰለው። የተስፋዬ ወደ ካቶሊክ ትምህርት ቤቱ መመለሱ የትምህርት ቤቱ አለቆችን፣ አስተማሪዎችንና ተማሪዎችን እጅግ በጣም ነበር ያስደሰተውና የተደረገለት አቀባበል እስካሁን ድረስ ይገርመኛል።"

ዶር ተስፋዬ በዓዲግራት በምተገኘው ካቶሊካዊት ት/ቤት በኩል ወደ ሮም Urbaniana University ተልኮ በፍልስፍና ጥናቱን በመከታተል በከፍተኛ ማዕረግ የዩንቨርስቲ ዶክተሬቱን እስኪያገኝ ድረስ ተማረ። "ዶር ተሰፋዬ በዶክትሪያል ድግሪ የተመረቀበት ጊዜ..." ይላሉ አቶ ግርማይ "...እኔም እሱ በተማረበት ዩንቨርስቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ስለነበርኩ ለዲግሪ ማሟያ የፃፈውን ፅሑፍ (ዲዘርተሽን) ያቀረበበት ቀን ተገኝቼ ነበር። ዲዘርተሽኑን ሲጽፍ የተከታተለው ዋና አስተማሪውና (Advisor) ሌሎች ብዙ የፍልስፍና ፋክልቲ አስተማሪዎች በተለያየ መልክ ላቀረቡለት ጥያቄዎች በማስረጃዎች የተደገፈ በቂና አስደሳች መልስ ስለሰጠ ከትልቅ ምስጋና ጋር "*Magna Cum Laude (ማኛ ኩም ላውደ)*" የሊቅነት ማዕረግ ሲቀበል ተገኝቼ ነበር።"

ዶር ተሰፋዬ ትምህርቱን እንደጨረሰ ወዲያውኑ ሀገሩን ለማገልገል፡ ለሕዝቡ ለመሥራት ወደ ሚወዳት ሀገሩ፡ ኢትዮጵያ ተመለሰ። ዶር ተስፋዬ ሥራ በሚፈልግበት ጊዜ ማንም የሚረዳው ሰው አልነበረውም። ከአንድ ዘመዴ ወይም ጓደኛዬ... ጋር ላስተዋውቅህ፣ ወዲያ... ሂድና እገሌ ልኮኛል በለው/በላት ሊልለት የሚችል ዘመድ ወይም ጓደኛ፣ ረዳት አልነበረውም። ስለዚህ ባከማቸው ትልቅ ዕውቀት የቀረቡለት ጥያቄዎችንና ቃለ መጠይቆችን በሚገባ ለመመለስ በመቻሉ በችሎታው በማስታወቅያ ሚኒስቴር ሥራ አገኘና በስነ ጽሑፍ ክፍል ተመድቦ ሠራ። ዋና ሥራውን ምርምር እያደረገ ለፕላኒንግ መሥሪያ ቤትና ለሌሎች ክፍሎች ጥናት ማቅረብ ነበር። እንዲሁም የአንዳንድ መጻሕፍትን ፍሬ ነገር (Summary) በአሕጽሮት እየጨመቀ ያቀርብ ነበር። በምርምር ክፍል ሲሠራ አንዳንድ ግኝቶችን በመጽሔትና ዕለታዊ ጋዜጦች ለማውጣት ይሞክራል። ሥርዓቱን የሚነኩ ከሆኑ አይታተሙለትም ። አንዳንድ ሥርዓቱን በሚመለከት ትችት የማያደርጉ ጽሑፎች ግን አልፎ አልፎ ታትመውለታል። ለምሳሌ በMarch 1970 ገደማ Ethiopian Herald ላይ "Zera-Yaqob the Philosopher and not the Emperor" በሚል አርዕሰት ያወጣው መጣጥፍ ነበር።

ዶር ተስፋዬ በተባለው መሥርያ ቤት በሠራበት ጊዜ የተለያዩ ሚንስትር መሥሪያ ቤቶችን የምሰጢር መዛግብት ለመመርመር ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶት ስለ ነበር አጋጣሚውን በመጠቀም የሀገራችን የፖለቲካ ሥርዓትና ቢሮክራሲው ምን ያህል የተበላሸ እንደነበረ በሚገባ የመታዘብና የመመልከት ዕድል ያገኘው። በዚሁ ጊዜ ዶር ተሰፋዬ በተጨማሪ በአባዲና ኮሌጅ የማታው ክፍለ ጊዜ ፍልስፍና ያስተምር ነበር።

ዶር ተሰፋዬ በአዲስ አበባ በሥራ ዓለም በቆየበት ጊዜ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ተራማጅ ምሁራን ጋርና የተማሪ ንቅናቄ መሪዎች ጋር፣ እንዲሁም ማታ የፍልሰፍና ትምህርት ለመከታተል ከሚመጡ የወታደርና የፖሊስ መኮንኖች ጋር ለመተዋወቅና አሰፈላጊ ግንኙነቶችን ለመመሥረት ቻለ። ይህም

በኋላ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕአፓ) ምሥረታና ማደራጀት ውስጥ ለተጫወተው ትልቅ ሚና አስተዋጽዎ ነበረው። በተለይ ኢ.ሕአፓን ካቋቋመው ተራማጅ ትውልድ ጋር ፅኑ ትውውቅ ሊገነባና ለድርጅቱ ምሥረታ ወሳኝ የነበረ ግንኙነት ሊፈጥር የቻለውም በነዚህ ዓመታት ውስጥ ነበር።

ዶር ተስፋዬ በ1964 ዓ. ም. እንደገና ወደ አውሮጳ (ስዊዘርላንድ) ሄደ። በዚህ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር የሄደው በኢትዮጵያ መካሄድ የነበረበትን አብዮት በሚመለከት በተለያዩ የወጭ አገሮች ከነበሩ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ጋር የትግል ዕቅዶችን ለመመካከርና ለመቀየስ ነበር። በኢትዮጵያ፣ በአውሮጳና አሜሪካ እየተመላለሰ በየአህጉሩ ተደራጅተው የነበሩ ቡድኖችን በማቀነባበር በኋላ ኢ.ሕአፓ የተባለ በ1964 ዓ. ም. የተመሠረተውን ድርጅት ማቋቋም በተመለከተ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። እንዲሁም በውጭ አገሮች የድርጅቱ የድጋፍ መሠረት የነበረው የኢትዮጰያ ተማሪዎች ማሕበራት በፌደራላዊ ቅርጽ ተደራጅተው ትግላቸውን እንዲያስተባብሩ፤ እንዲያቀናጁ በማድረግም ትልቅ ሚና ተጫውቷል።

የ1966ቱ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ወቅት ጊዜ ዶር ተስፋዬና ሌሎች ኢ.ሕአፓን የመሠረቱ ተራማጆች የዓፄ ኃይለሥላሴን መንግሥት ለመለወጥ የትጥቅ ትግልን የጨመረ ዝግጅት በማደረግ ላይ ነበሩ። የ1966ቱ አብዮት እንደተቀጣጠለ የዓፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሚንስትሮችን በመለዋወጥና ሕገ-መንግሥቱን አሻሽላለሁ፣ ዴሞክራሲም እፈቅዳለሁ ዓይነቱ ግርግር ውስጥ ገባ። በዛን ጊዜ ዶር ተስፋዬ በፃፈው የድርጅቱ መግለጫ ውስጥ እንደ አቶ ግርማይ አባባል የሚከተለው ይገኛል "ዝግጅታችን በግድ ለሕጋዊም፣ ከሕግ ውጭ ለሚደረገው ትግል ጭምር መሆን አለበት፤ የሕገ መንግሥቱ ለውጥ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሕጋዊ ትግል የሚፈቅድ ከሆነ በሕግ እንታገላለን፤ ካልፈቀደ ግን በሕግ የተሰየመውን አመጽ በእውነተኛው ሕግ፤ በሕዝብ ሕግ ለመተካት እንታገላለን።"

ዶር ተሰፋዬ በሰኔ ወር 1966 ወደ አገር ቤት ገባ። ጊዜው በአብዮቱ እንቅስቃሴ በአስተባባሪ ኮሚቴነት ሲሰራ ቆይቶ እራሱን እያጠናከረ ብቅ ያለው ወታደራዊ ደርግ በአዋጅ የተመሠረተበትና በግልፅ በመውጣት በዓፄው አገዛዝ ተጠያቂ ያላቸውን ሚንስትሮች፣ ከፍተኛ መኮንኖች፣ ባላባቶችንና መኳንንቶችን የሚያሥርበት ወቅት ነበር። በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ አቶ አክሊሉ ሀብተወለድን ተክተው ጠቅላይ ሚንስተር ተሹመው የነበሩ ልጅ እንዳልካቸው መኰንን በልጅ ሚካኤል እምሩ የተተኩበት ጊዜም ነበር። ልጅ ሚካኤል በስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ልዑክ በነበሩበት ጊዜ ዶር ተስፋዬ ጋር ተዋውቀው ስለነበር ዶር ተስፋዬ ወደ አገር ቤት እንደገባ ፈላልገውት የመሬት ይዞታ ሚንስትር እንዲሆን ጠይቀውት ዶር ተሰፋዬ ግን ሌላ፡ ልጅ ሚካኤል ያላወቁት ዕቅድ ስለነበረው ምክንያት ፈጥሮ በከበሬታ ሳይቀበላቸው ቀረ። ሆኖም ግን በመሬት ይዞታ ውስጥ ተመድቦ በትግራይ ክፍለ ሀገር እንዲሠራ ከተፈቀደለት ለመሥራት ዝግጁ እንደሆነ ነገራቸው። እርሳቸውም ሀሳቡን ተቀበሉት። አፀደቁለት። ዶር ተሰፋዬ በትግራይ እንዲመደብ የፈለገው በዓሲምባ ተመሥርቶ ከነበረው ከኢ.ሕአፓ ሠራዊት (ኢ.ትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢ.ሕአሠ)) ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች እንዲያመቸው ነበር። አሲምባ አካባቢ ከአለው ወታደራዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ የዶር ተስፋዬ የትውልድ ሥፍራ በመሆኑ ለኢ.ሕአፓ ሠራዊት የኢ.ሕአሠ ዋና ቤዝ ይሆን ዘንድ ለተደረገው ምርጫ አስተዋጽዎ አድርጓል።

ዶር ተስፋዬ አንድ ዓመት የሚሆን ጊዜ በተሰጠው የሥራ መስክ እየሠራና በሀገሪቷ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሕግ እየተዘዋወረ ከሌሎች ጓዶቹ ጋር በሕቡእ ህዝቡን በኢሕአፓ ጥላ ሥር በማደራጀትና ትግሉን በመምራት ላይ እያለ የዶር ተስፋዬ ማንነትን የሚያውቁ ግለሰቦች ኢሕአሠን ከድተው ወደ ደርግ መግባታቸውን ስላወቀ የመንግሥት ሥራ ትቶ ቀዳሚ ሥራውን ለትግሉ በመስጠት፤ "የትግሉ ነው ሕይወቴ" በማለት ኢሕአፓን የማደራጀትና የመምራት ኃላፊነቱን  በሕቡእ ያከናውን ያዘ።

"ዶር ተስፋዬ ደበሳይን የማውቀው ወደ ሠራዊቱ አሲምባ ሲመጣ ነው።" ያሉት የኢሕአፓ/ኢሕአሠ መሥራች አባል አቶ ፀሐዬ ረዳ "በመጀመሪያ የመጣ ወቅት ቤተሰቦቹን ኢያለሁ በማለት የመንግሥት መኪና ይዞ እንደመጣ አስታውሳለሁ። በዚህ ጊዜ አመጣጡ ኢሕአፓን ለማወጅ ሊደረግ ለታሰበው ኮንፈረንስ ብርሃነ መስቀል ረዳን ከአሲምባ ለመውሰድ በመምጣቱ የነበርነውን ጥቂት የሠራዊት አባላት ለማወያየት ጊዜም አልነበረውምና ለሁለተኛና ሦስተኛ ጊዜ አሲምባ ሲመጣ ነው በሚገባ የተወያየነውና ባህሪሁንም በመጠኑ ያየሁት" ይላሉ አቶ ፀሐዬ በመቀጠል "ተስፋዬ ከጅምር እንጠቀምበት የነበረውን የሠራዊቱን ሕግና ደንብ በመጠኑም ቢሆን እንዲሻሻል ያደረገና ሠራዊቱን በጋንታ በጋንታ በማወያየትና የሠራዊቱንም አዛዥ ክፍል (Command Unit) ያዋቀረና ያጠናከረ ብቃት ያለው አመራር ሲጪ ነበር።"

"ዶር ተስፋዬ ከሻቢያ ጋር የተደረገውን ስብሰባ ለመምራት ለሦስተኛ ጊዜ ወደ አሲምባ መጥቷል። በዚህ ስብሰባ ላይ ሻቢያ ውይይቱን ከመደበኛ አካሄድ ውጭ በጥያቄ መልክ በማካሄዱ ይቀርቡ ለነበሩ ጥያቄዎች ዶር ተስፋዬ እንደ ቡድኑ መሪነት እኔ ልናገር ባይ አልነበረም። ይቀርቡ የነበሩ ጥያቄዎችን በወቅቱ አብረን ለሄድነው ልዑካን ለእኔ፣ ለፀጋዬ ደብተራው፣ ለጋይምና ግሩም በየተራ እንድንመልስና ማብራሪያ እንድንሰጥ በመጋበዝ ምን ያህል እራሱን ከፍ ከፍ የማያደርግና ልታይ ልታይ የሌለበት እጅግ በጣም ዴሞክራቲክ ባህሪ ያለው የኢሕአፓ መሥራች አባልና ከምሥረታው ጀምሮ የፓርቲው ፖሊት ቢሮ አባል፤ ችሎታና ዕውቀቱን ለሀገርና ሕዝብ የሰጠ የያ ትውልድ አባል ነበር።" አቶ ፀሐዬ ረዳ

ኢሕአፓ የፖለቲካ ፕሮግራሙን በነሐሴ 27 ቀን 1967 ዓ.ም. ለሕዝብ በማሳወቅና እራሱን ይፋ በማውጣት የደርግን ፋሽስታዊ አገዛዝ በማንኛውም መንገድ በመታገል ለማስወገድና በሀገሪቷ ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት በመመስረት የሕዝቡን በሀገሩ ገደብ የሌለውን ዴሞክራሲያዊ መብቱን በማወቅ ለሀገር ልማትና ዕድገት መሠረት የሆነ ሕዝባዊ ሥርዓት ለመመስረት የታገለ የመጀመሪያው ቀዳሚ የሕዝብ ፓርቲ ነበር። የደርግ አገዛዝ የኢሕአፓን ሕዝባዊ መሠረት ሊያናጋና እንቅስቃሴውንም ሊያጨልም የሚችለው በየትኛውም የሀገሪቷ ክልል ዘርና ሃይማኖት፣ ዕድሜና ፆታ ሳይለይ ያሳተፈና ለትግሉ ከዳር ዳር ያንቀሳቀሰን ፓርቲ ማንንም ሳይለዩ በጥርጣሬ፣ በመሰለኝ፣ በቅናት፣ በቂም በቀል ወዘተ. የታገዙ ግድያዎችን "በማር" በተለወሱ መርዘኛ አዋጆችና መግለጫዎች <u>***ግድያን በዘመቻ***</u> ለማካሄድ፡ ነፃ የመግደል መብትን በአጠገቡ ለተኮለኮሉት ቡድኖችና በየቀበሌው ላደራጃቸው የአብዮት ጥበቃዎች በመስጠት በመላ ሀገሪቷ ላይ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር በማወጅ አንድ ትውልድን ያለምንም ሕግ ያጠፋ አገዛዝ ነበር። ለዚህም ደርግ በ1969 ዓ.ም. ለተጀመረው የቤት ለቤት የአሰሶ መደምሰስ ዕቅዱ የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤትን በጉያው በተወሸቀው መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የበላይ ተቆጣጣሪነት በአዋጅ በማቋቋም ሦስት አሰሳዎችን አካሂዷል። የመጀመሪያው ህዳር 1969 ዓ.ም. ሲሆን ሁለተኛው ለሦስት

ቀን የተካሄደው መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. የተካሄደው ሲሆን ሶስተኛውና የመጨረሻው ሚያዝያ 1969 የተካሄደውና መኢሶንም እራሱ የወጠነው ጥቃት ሰለባ የሆነበት አሰሳ ነበር።

የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤት እና መኢሶን የአስሶ መደምሰስ ዘመቻ በተግባር ለመተርጎም ሁለተኛው የቤት ለቤት አሰሳ መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. ተጀመረ። የአብዮት ጥበቃ አባላት፣ ጦር ሠራዊቱ፣ ቀበሌዎች፣ የሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት በተለይም መኢሶንና ሌሎች በደርግ ዙሪያ የተሰበሰቡ ቡድኖች አባላት በቤት ለቤት አሰሳው ተካፍለዋል። ለሶስት ተከታታይ ቀናት የተካሄደው አሰሳ ሕዝቡ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ እንዳይንቀሳቀስ በወጣ የደርግ ተከታታይ መግለጫ የታገዘ ነበር።

ከኢሕአፓ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ ወጣቶችና ሠራተኞች ሁሉ በጅምላ ታሰሩ። በ1969 ዓ.ም. በየካቲት ወር መጨረሻ አካባቢ በርካታ የኢሕአፓ አመራር አባላት አዲስ አበባን ለቀው መውጣታቸው ቢታወቅም ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይ የአዲስ አበባው የኢሕአፓ መዋቅር ውስጥ ያሉ አባላትን በእንዲህ ያለ ቀውጢ ጊዜ ትቶ መሄዱ ለሕሊናው ስለከበደው ለሀገሩና ለሕዝቡ ብሎም ለትግሉ የሰጠውን ሕይወቱን፤ በፍጹም እምነቱ ሊተገብር፤ ማንኛውንም መከራና ስቃይ እራሱን ከፍ ሳያደርግ እንደ ሌሎች የኢሕአፓ አባላት አብሮ ሊመክትና ሊታገል ወሰነ።

እንደ አቶ ክፍሉ ታደሰ «ያ ትውልድ» ቅጽ II ገለጻ "መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም. ዶር ተስፋዬ ደበሳይና ጓደኛው በሪሁን ማርዬ የደርግ የቤት ለቤት አሰሳ መስሪያ ቤቶች ላይ ትኩረት ስላላደረገ አምባሳደር ትያትር አጠገብ ወደሚገኘው የኪዳኔ በየነ ሕንጻ አመሩ። ሕንጻውን የመረጡት የበሪሁን ባለቤት የምትሰራበት ቢሮ በመሆኑና እዚያ በመሆን አሳሹን ቡድን ላማሳለፍ በማቀድ ነበር። ዶር ተስፋዬ በዕለቱ ይጓዝባት የነበረችው መኪና በተክለ ሃይማኖት አካባቢ ስታልፍ የመኢሶን መሪ አባላት በወቅቱ አሰሳ ያደርጉ ስለነበር መኪናው ውስጥ ዶር ተስፋዬን መለየት እንደቻሉ መኪናውን መከተል ይጀምራሉ።" ይላል።

ተስፋዬና በሪሁን የሚከተላቸውን ሳይጠራጠሩ ወደ ሕንጻው ውስጥ እንደገቡ ተስፋዬ በመኢሶን አባልነት የሚጠረጠር አንድ ሰው ስላየ ሕንጻውን ለቆ ለመሄድ ወዲያው ወሰነ። ዶር ተስፋዬ የሕንፃውን ደረጃዎች ወርዶ መሬት ሲደርስና የመኢሶን አሳሽ ቡድን ወደ በሩ ሲጠጋ አንድ ሆነ። ወዲያውም አሳሹ ቡድን ተኩስ በመክፈት ከፊት ለፊት ይመራ የነበረውን በሪሁን ማርዬን ከመቅጽበት ገደለው። በዚህ ጊዜ ዶር ተስፋዬም ፊቱን አዙሮ የፎቁን ደረጃዎች በሩጫ በመውጣት ስድስተኛው ፎቅ እንደደረሰ በአለው መስኮት ቁልቁል ወደ መሬት ራሱን በመወርወር ተፈጥፍጦ ሞተ።

"ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ
ለአዲስ ሥርዓት ልምላሜ
ፍጹም ነው እምነቴ
ለትግሉ ነው ሕይወቴ" ን      በደሙ ጻፈ።

ልጆቹን ያዘመራቸውን "ለዘመናት" በተግባር አሳያቸው። "ቀጥሉ!" አላቸው፡ "አታቁሙ!"፡ "በሉ!"፡

"ልጓዝ በድል ጎዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና" ።

*የዶር ተስፋዬን ፈለግ በመከተል በመኢሶንና ደርግ ገዳዮች እጅ ከመውደቅ ይልቅ ሕይወታቸውን ለትግሉ በመስጠት አኩሪ ጀግንነት አስመዝግበው እስከወዲያኛው ያሸለቡ የኢሕአፓ ሰማዕታት በርካታ ናቸው። እንደ አቶ ክፍሉ መጽሐፍ ያ ትውልድ ቅጽ || አገላለጽ "የተስፋዬ ሞት፡ በኢሕአፓ ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ ደጋፊ ትውልድ ላይ መኢሶን ያሳረፈው ክፉና ገዳይ በትር ነበር።"*

*ዶር ተስፋዬ ደበሳይ፤ በዓፄነታቸው ሳይኮፈሱ፡ ዳር ድንበሬን ብለው፡ ለሀገር አንድነትና ክብር ከድርቡሽ ወራሪ ጋር ሲፋለሙ የተሰዉት ዓፄ ዮሐንስ፣ እጅህን ስጥ አለኝ…ለጠላት? ለወራሪ? ለእንግሊዝ? ብለው ለሀገር ክብር እራሳቸውን በመሰዋት ታሪክ አስመዝግበው ያለፉት ዓፄ ቴዎድሮስ፣ ለጣሊያን ፋሺስት ወራሪ ሕዝቡ እንዳይገዛ ገዝተው የሀገራቸውን ክብር በደማቸው የፃፉት አቡነ ጴጥሮስ፣ ወዘተ አርሂያ በመከተል ለሀገርና ለሕዝብ መብት የሚደረግ ተጋድሎ መስዋዕትነት ሊከፍሉ ዝግጁ በሆኑ አመራርና አባላቱ ጽናት መሆኑን አካሉን የከሰከሰ፡ ደሙን ያፈሰሰ ጀግና የኢሕአፓ መሪና ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ነበር።*

*ዶር ተስፋዬ የፓርቲው የርዕዮተ ዓለም ግንባር ቀደም አራማጅ፣ አደራጅ፣ የፖለቲካ ጠቢብና መሥራች አባትም ነበር። ለዝናና ለታዋቂነት ቁብ ያልነበረው ተስፋዬ፤ በሌላው ቀርቶ በኢሕአፓ አባላት እንኳን በጥቂቶች ነበር የሚታወቀው። ይሁንና በቅርብ በሚያውቁት ጓዶቹ መካከል ከማንም በላይ የሚከበር ነበር። ተስፋዬ ብዙ አይናገርም፡ መናገር ሲጀምር ግን በአካባቢው ያሉና የሚሰሙት ሁሉ ከአንደበቱ የሚወጣውን እያንዳንዱን ቃል እንዲያደምጡ የማስገደድ ኃይል የተላበሰ ነው። ተስፋዬ በማኅበራዊ ሕይወቱ እውነተኛ፣ ግልጽና ትሁት ሰው ነበር። ጥልቅ የዴሞክራሲና የፍትህ ስሜት የተዋሃደው ሰውም ነበር። በፖለቲካ አስተሳሰቡ ውስብስብና የረቀቀ ከመሆኑም ሌላ፡ ከማንም በላይ ሩቅ ሀሳቢ እንደነበር የሚያውቁት ሁሉ ይመሰክራሉ።*

*"ማንም ሰው አይናገረው እንጂ፤…" እንደ ያ ትውልድ ቅጽ || አባባል "ማንም ሰው አይናገረው እንጂ፤ ከተስፋዬ ሞት በኋላ ኢሕአፓ የወትሮው ኢሕአፓ እንደማይሆን አውቆታል። ኢሕአፓ በተስፋዬ ሞት፤ ሕይወትና ግርማ ሞገስ የሚያጎናጽፈውን መንፈሱን አጣ። ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ጥብቅ መሪውን በሚፈልግበት ጊዜ፤ እንደ ተስፋዬ አርቆ አስተዋይና መንገድ አመላካች ሰው በሚሻበት አስቸጋሪ ወቅት ኢሕአፓ መሪውን አጣ።"*

*ከደሀ ቤተሰብ ተወልዶ፤ ከመርፌ ቀዳዳ በጠበበች ዕድሉ ተጠቅሞ የዘመናዊ ትምህርት ዕድልን በማግኘት በፍልስፍና የዶክተሬት ማዕረግኑት የተጎናጸፈው ዶር ተስፋዬ ዕውቀቱን ለሀገሩና ለድሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገትና ብልጽግና የዘረጋውን ምኞቱንና ተስፋውን ሳያይ በጅምር ተቀጨ። "የተስፋዬ ዛፉ፤ ሲከረከም ቅርንጫፉ" እንዳለው ገጣሚ የተስፋዬ ተስፋ በተስፋ ቀረ። ብርሃን ዐይኑን ከደነ። በአጭር ተቀጨ። ተቀበረ።*

*ዶር ተስፋዬ ባለትዳርና የአንዲት ሴት ልጅ ሐምራዊት አባት ነበር። ሐምራዊት የአባቷን ጣዕም ሳታውቅ በሕጻንነታቸው ደርግ ወላጆቻቸውን ከበላባቸው፤ የአባት ወይም የእናት ወይም የሁለቱንም ጣዕም ሳያጣጥሙ፣ ሳያውቁ ካደጉት፤ የወላጆቻቸው አኩሪ ታሪክ እንኳ ያልተዳሰሰላቸው በርካታ የትላንት ሕፃናት የዛሬ ወጣቶችና ጎልማሳዎች ውስጥ ከሚመደቡት ናት።*

«ያ ትውልድ ተቋም» ከተነሳበት ዓላማ አንዱ የዚያን ትውልድ ሰማዕታት መዘከርና ታሪካቸውን ለትውልድ ማስተላለፍ በመሆኑ የዶር ተስፋዬ ደበሳይን 36ኛ የሙት ዓመት መዘክር ስናስታውስ በጥልቅ ሐዘን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና ኢሕአፓ አንድ ሁነኛ መመኪያውንና መሪውን ያጣበት ቀን መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም.። ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደነቷን ጠብቃ የልጆቿ ሙብት የተከበረባትና ለሀገር ብልጽግናና ለልማት የተከፈለው የያ ትውልድ ሰማዕታት ደም ከንቱ እንደማይቀርና ሁሌም በትውልድ ሲዘከር፡ ሲታወስ እንደሚኖርና የትግላቸውም ፍሬ ኢትዮጵያ ሀገራችንንና ልጆቿን ከፍ ከፍ እንደሚያደርጋት እምነታችን የጸና ነው።

"ዶር ተሰፋዬን የማውቀው በሶሰት የተለያዩ አጋጣሚዎች ነው። መጀመርያ፦ በዓዲግራት ኣቶሊካዊት ት/ቤት እኔ የመጀመርያ ደረጃ ተማሪ ሁኜ እሱ ደግሞ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኖ፤ ሁለተኛ፦ በጣሊያን አገር እኔ የመጀመርያና የሁለተኛ ዓመት የዩንቨርስቲ ተማሪ ሁኜ ዶር ተሰፋዬ ደግሞ የድረ ምረቃ (Post Graduate) ተማሪ ሆኖ፤ ሶስተኛ፦ በአዲስ አበባ በሥራ ዓለም ቆይቶ እንደገና ወደ አውሮጳ በተመለሰ ጊዜ" ያሉን አቶ ግርማይ ተስፋ ጊዮርጊስ፡ የዶር ተስፋዬን 36ኛ ዓመት የሙት ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ ይህን አጭር የሕይወት ታሪኩን ለማዘጋጀት ላደረጉልን ከፍተኛ ትብብር «ያ ትውልድ ተቋም» የከበረ ምሲጋናችንን እያቀረብን ሌሎችም የአቶ ግርማይን አርሃያ በመከተል በምታውቁት ታሪክ ላይ ትብብራችሁ ቀና ይሆን ዘንድ በዚህ አጋጣሚ «ያ ትውልድ ተቋም» መልዕክቱን ያስተላልፋል።

ይህንን የዶር ተስፋዬ ደበሳይን የሕይወት ታሪክ በመጠኑም ቢሆን ለመጻፍና ማንነቱን ለመግለጽ ለአደረግነው ጥረት ከፍተኛ ትብብር ያደረጉልንን አቶ ግርማይን እንዳመሰገንን፤ ለዚህም ስኬታማነት በሩን የከፈቱልንን ባለቤቱ የነበሩትን ወ/ሮ ፍቅርተ ገ/ማርያምንና አንድዬ ልጁን ወ/ሪት ሐምራዊት ተስፋዬን በያ ትውልድ ወገኖቻችን፡ በኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝባችን እንዲሁም በ«ያ ትውልድ ተቋም» ስም ከፍተኛ ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

በመጨረሻም ከኢሕአፓ መስራች አባላት አንዱ የነበሩትና በተለይ የኢሕአሠ ጥንስስ መሠረት ለመጣል የመጀመሪያው የሠራዊቱ መሥራች አስኳል የነበሩት አቶ ፀሐዬ ረዳ፡ ስለ ዶር ተስፋዬ ደበሳይ ያላቸውን እውቅናና በተለይ በአሲምባ ያላቸውን ትዝታ በማውሳት ላደረጉልን ቀና ትብብር «ያ ትውልድ ተቋም» ወደር የሌለውን ምስጋናውን ያቀርባል።

የዶር ተስፋዬ ደበሳይ በተለይ በኢሕአፓ ውስጥ ያለውን ሚና፣ ያበረከተውን አስተዋጽዎና የትግል ተሳትፎ ከሌሎች ትብብር ለማግኘት ያደረግነው ጥረት ባለመሳካቱ የተሰማንን ቅሬታ እየገለጽን አሁንም በድጋሚ <u>የኢሕአፓ ታሪክ የሀገርና የሕዝብ እንደመሆኑ ጽፈው ሊያስነብቡ ፈቃደኛ ባልሆኑ፡ ሌሎች ሲጽፉም ጸጉራቸው በሚቆመው "እኛ ብቻ" ባዮች ታሪክ እንዳልሆነ</u> «ያ ትውልድ ተቋም» በድጋሚ ሊያደምቀውና ሊያሰምርበት ይወዳል።

*ያ ትውልድ ተቋም*
*መጋቢት 15 ቀን 2005 ዓ.ም.*

<u>ዋቢ ጽሁፎች</u>

- ቃለ መጠይቅ፡ ከአቶ ግርማይ ተስፋ ጊዮርጊስ ጋር
- ቃለ መጠይቅ፡ ከአቶ ፀሐዬ ረዳ የኢሕአፓ መሥራች አመራር አባል
- «ያ ትውልድ» ቅጽ ሁለት ክፍሉ ታደሰ፤ 1991 ዓ.ም. ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች ሰሜን አሜሪካ